“በጥበበኛ አዛዥ የሚመራ ጦር ሳይታሰብ ግድቡን ጥሶ በሚጎርፍ ደራሽ ውሃ ይመስላል። ደራሽ ውሃ ከፍተኛ ቦታን እየለቀቀ፣ ወደ ዝቅተኛ ቦታ እያዘቀዘቀ፣ ዝቅዝቅ በመጉረፉ በሚያገኘው እየጨመረ የሚሄድ እንድርድረት (increasing momentum) እንቅፋቶቹን እየጠራረገ ረባዳን ያጥለቀልቃል። በጥበበኛ የጦር አዛዥ የሚመራ የጦር ሠራዊትም የጠላትን ጠንካራ ጎን እየራቀ፣ ደካማ ጎኑን እየሰነጠቀ፣ እየጎለበተ በመትመም፣ የጠላት ጦር ያልሰፈረበትን የጠላት ግዛት እንበለ ውጊያ በመቆጣጠር ይንቦራቀቅበታል። ደራሽ ውሃ ወደ መዳረሻው የሚወንዘው አወናነዙን ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር እያዛመደ ፍጥነቱን፣ ስፋቱንና ጥልቀቱን በመለዋወጥ እንደሆነ ሁሉ፣ በጥበበኛ የጦር አበጋዝ የሚመራ ሠራዊትም ወደ ግቡ (goal) የሚያመራው የጠላቱን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ትልሙን (strategy) እና ስልቱን (tactic) እንዳስፈላጊነቱ በመለዋወጥ ነው።”

ሰንሹ (Sun Tzu)

“ጦርነት ማለት በሸወዳ (deception) ላይ የተመሠረተ መጨፋጨፍ ማለት ነው። በመሆኑም ዋናው የድል ቁልፍ የሸወዳ ክሂሎት ምጥቀት ነው። የአጉል ጀብደኝነት ትርፉ አላስፈላጊ መስዋዕትነት ነው። ስለዚህም ጠንካራ ስትሆን ደካማ፣ ደካማ ስትሆን ጠንካራ፣ ዝግጁ ስትሆን አልዝግጁ፣ አልዝግጁ ስትሆን ዝግጁ፣ ሩቅ ስትሆን ቅርብ፣ ቅርብ ስትሆን ሩቅ፣ በግራ ስትሆን በቀኝ፣ በቀኝ ስትሆን በግራ መስለህ ለጠላትህ ታይ። ጠላትህን እንቁ አሳይተህ እነቀው።”

ሰንሹ (Sun Tzu)

የጦቢያ ሕዝብ ካብናቶቹ (ማለትም ካባቶቹና ከእናቶቹ) በቀሰመው ባያሌ የጦር አውድማወች ላይ በተፈተነ፣ አያሌ አሸብራቂ ድሎችን ባጎናጸፈ ዘመን ጠገብ አራት ማዕዘናዊ የጦርነት ጥበብ (ፊታውራሪ፣ ጃዝማች፣ ግራዝማች፣ ደጃን) የተካነ ነፍጠኛ በመሆኑ፣ ይህን የጦርነት ጥበብ በሌሎች አገሮች (በተለይም ደግሞ በቻይናና በሩሲያ) የጦርነት ጥበቦች ካዳበረው ማናቸውንም ጦርነት ባሸናፊነት የመወጣት ዕድሉ ከፍተኛ ይሆናል። የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማም ይሄው ነው፣ የሰንሹን የጦርነት ጥበብ መሠረታዊ ሐሳቦች ለሰፊው የጦቢያ ሕዝብ ማስተዋወቅ።

**ዋጋው 20.00 ዶላር**

# የሰንሹ የጦርነት ጥበብ




## በ

## መስፍን አረጋ

